ጠልሰም ጥንቆላ ነው የሚል ምላሽ “ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት” ማግኘቴ እጅጉን አሳዝኖኛል ምክንያቱም እንደኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ልጅ ነቴም ሆነ ለታሪኩ እንደሚቆረቆር ወጣታም ይህ እጅጉን የሚያሳዝን ምላሽነው፡
፡ በጣም ያስገረመኝም የተጠቀሱት መጽሀፍት የጥንቆላ ናቸው የሚል ተጨማሪ ህጸጽ ያለበት ምላሽም ማግኘቴ ነው ምላሹም በከፊል እንደሚከተለው ነው . . . . . . .
“ ጠልሰምም፡ ከእነዚሁ፡ የባዕድ አምልኮ መሣሪያዎች አንዱ ስለኾነ፡
በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ ጨርሶ ተቀባይነት የለውም። በእ-ጦማርዎ ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትመጻሕፍትም፡ የዲያብሎስ አገልጋዮች የኾኑ "የቤተ ክህነት ወገኖች ነን!" የሚሉ አሳሳቾች፡ ለኃጢአት ሥራ የሚጠቀሙባቸውሊኾኑ ስለሚ ችሉ፡ ብርቱ ጥናትና ምርምር ሊደረግባቸው፥ በጥንቃቄም ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው። ሕዝቡን በጥንቆላ፥
በሰይጣንና በባዕድ አምልኮ፡ ቀሥፈው ይዘው እንደሚሣቅዩበት፡ "ዐውደ ነገሥት" እን ደሚሉት መጽሓፍ ማለት ነው “
ጠልሰም ከኢትዮጵያዊነታችን ጋር የተገናኘ ሰፊ ምስጢራት አለው ለዚህም ነው በርካታ ሺህ ጥንታዊ መጽሀፍቶቻችንም ሆነየገዳማቶቻችን የውስጥ ስእላት በጠልሳማት ያሸበረ ቁት፡፡
አባቶቻችን የነበራቸውን የጠልሰም ጥበብ በሁለት መልኩ ማየት ይገባናል አንደኛው የቀ ደሙት አባቶቻችንን ምግባር እናጥበብ ይዘው ለተፈቀደለት ዓላማ ማለትም ለመንፈሳዊ ተግባራት የሚጠቀሙበት አባቶች አሉን እንዲሁም ለስጋቸው ያደሩስግብግብ ሰዎች ለ ስጋዊ ጥቅማቸው ሲሉ ይህን ጥበብ ለማይገባው ዓላማ ይጠቀሙበታል፡
፡ በመሆኑም እንደ አንድ የታሪክጸሀፊም ሆነ ኢትዮጵያዊ ክፉን ከበጎው በመለየት ትው ልዱን ማሰተማር እንጂ በግርፉ የ...ጠልሰም ጥበብ ጥንቆላ ነው ብሎማጣጣል ተገቢ አ ይደለም፡
፡ በተጨማሪም የጥንቆላ መጽሀፍት ናቸው ያላችሁት መጽሀፍት በተለያዩ ገዳማት ውስ ጥ ማለትምእንደ ዋልድባ ባሉ ገዳማት ውስጥ አሁንም አገልግሎት እየሰጡ ያሉ መጽሀ ፍት ናቸው፡፡
በመሆኑም ይህን መልእክት የምታነቡ ሁሉ ጠልሰም የቀደሙት አባቶቻችን ጥበብ እንደ ሆነ ለመረዳት በተለያዩ ቦታዎችየሚገኙትን ቅዱሳን ገዳማትና ጥንታዊ መጽሀፍቶቻችንን ማገላበጥ በቂ ነው፡፡
በስተመጨረሻ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ማንጸባረቅ የሚገባን ሳንጨምር ሳንቀንስ መ ሆን ይገባዋ እያልኩኝ ጠልሰምየቀደሙት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንን የጥበብ ውጠየት የነበረ ለዘመኑም ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ እንደነበር ማስረጃዎችንማቅረብ የምችል መሆኔን እገልጻለሁ፡፡

**እግዚአብሔር ያክብርልኝ !!!!**

**ራፋቶኤል**